

# ጴጥሮስና ዶርቃስ

- ዶርቃስ ማለት ሚዳቋ ማለት ነው። ይህ የአንዲት እግዚአብሔርን የምትፈራና ኢዮጴ በሚባል ስፍራ ትኖር የነበረች ሴት ሰም ነው። በተጨማሪም ጣቢታ በመባል ትታወቃለች። መበለቶችንና ድሆችን በመርዳት የታወቀችና በጣም ርህሩህ ሴት ነበረች።

- እግዚአብሔር ለመበለቶችና ለድሆች የሚያስብ አምላክ ነው።. በጥንት የመፅሐፍ ቅዱስ ዘመን አንዲት ሴት በሏ ከሞተባት ሌላ የገቢ ምንጭ አይኖራትም። ስለዚህም የግድ በሌሎች ሰዎች ላይ መደገፍ ይኖርባታል። ይህ ሁኔታ ዛሬም እንኳን በአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች የሚታይ እውነት ነው።

- በዚያን ጊዜ የነበረው ሕግ የአንዲት ሴት ባል ቢሞት መሬቱን የሚወርሰው ወንድ ልጁ ነበር። ባሏ የሞተባት ሴትም ወራሽ የሆነው ወንድ ልጇ ካልረዳት ሌላ ተስፋ ልታደርገው የምትችለው ማንም ሰው አይኖርም። ወንድ ልጅ ከሌላት ደግሞ የባሏን መሬትና ሌሎች ንብረቶች ታጣለች። ወይንም ከባሏ ዘመዶች ሌላ ሰው ማግባት ይኖርባታል። አለበለዚያ ግን የባሏን ሀብትና ንብረት በፍፁም ማግኘት አትችልም። ይህንን ሀሳብ በደንብ መረዳት የምንችለው በመፅሐፈ ሩት ላይ ስለ ሩትና ስለ ቦኤዝ ታሪክ ስናነብ ነው።

- እግዚአብሔር አይሁዳውያን ለድሆች እንዲያስቡ ነግሯቸዋል። በእርሻቸው ዳር ያለውን ሰብል እንዳይሰበስቡና ድሆች መጥተው እንዲለቅሙ መተው እንዳለባቸው አዟቸዋል። እንዲሁም እህል አንዴ ከተሰበሰበ በኋላ ትርፍራፊውን ለመሰብሰብ ሁለተኛ ዙር ወደእርሻቸው መመለስ እንደሌለባቸው ነግሯቸዋል። ለድሆች መተው ይኖርበታል።

- በየሶስት ዓመቱ የእህሉ አንድ አስረኛ(አስራት) ለድሆች ይሰጥ ነበር። እንዲሁም በየሰባት አመቱ እዳ ይሰረዛል። በዚህም ሰዎች ሁሉንም ነገር እንደአዲስ ይጀምራሉ።

- በአዲስ ኪዳን ያዕቆብ ሲፅፍ የንፁሕ ሃይማኖት አንደኛው መለያው መበለቶቸንና ወላጅ አልባዎችን መንከባከብ መቻሉ ነው። ለድሆች የሚያስቡ እግዚአብሔርን ያስደስቱታል፤ በእርሱ ዘንድም ተቀባይነት አላቸው። ይህንን የማያደርጉ ግን እግዚአብሔርን ያሳዝኑታል።

- ዶርቃስ ኢዮጴ በምትባል የወደብ ከተማ ትኖር ነበር። (ከዚህ በታች ያለውን ስዕል ተመልከቱ።) ዶርቃስ የፍቅር ሰው ስትሆን ለሌሎች የምትራራና በተለይም ድሆችን መርዳት የምትወድ ሴት ነበረች።  . መበለቶች በክረምት ወራት እንዳይበርዳቸው በማሰብ የሚያሞቃቸው ልብስ ሰርታ ትሰጣቸው ነበር።

- አንድ ቀን ታመመችና ሞተች። ወዳጆቿ እጅግ በጣም አዘኑ። በጣም የሚወዷት ጓደኛቸው ሄዳለችና።

- ጴጥሮስ ተአምራትን እንደሚያደርግና የታመሙ ሰዎችን እንደሚፈውስ ሰምተዋል። በዚህን ጊዜ ከሐዋርያት መካከል አንዳቸውም ሙታንን አላስነሱም። የዶርቃስ ወዳጆች ጴጥሮስ ያንን እንደሚያደርግ አመኑ። ስለዚህም ሁለት ሰዎች ልዳ ወደሚባለውና ጴጥሮስ ወዳረፈበት አካባቢ ሄዱና ጠሩት።

- ጴጥሮስም ከሰዎቹ ጋራ ወደ ኢዮጴ ተጓዘ። እዚያ እንደደረሰም ወዳጃቸውን ዶርቃስን በላይኛው ክፍል ውስጥ አስቀምጠዋት ነበር። ክፍሉም ዶርቃስ የሰራችላቸውን የተለያዩ ልብሶች ይዘው እያሳዩ በሚያለቅሱ መበለቶች ተሞልቶ ነበር። እያንዳንዱ ስፌት ታማኝነትዋንና ፍቅሯን ያስረዳ ነበር።

- ጴጥሮስም ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ ካዘዛቸው በኋላ በጉልበቱ ተንበርክኮ መፀለይ ጀመረ። እግዚአብሔርንም ሕያው እንዲያደርጋት ለመነው። " ከዚያም "ጣቢታ ተነሺ!" አላት።

- አይኖቿን ከፈተች። ጴጥሮስንም አየችው። ተቀመጠችም። በእጁ ይዞ አስነሳት፤ ቆመችም።

- ከዚያም ጴጥሮስ ሰዎቹ ወደ ክፍሉ ውስጥ እንዲገቡ ፈቀደላቸው። እነርሱም ወዳጃቸው ሕያው ሆና አዩአት። እጅግ በጣምም ደስ አላቸው።      ወሬውም በፍጥነት በኢዮጴ ከተማ ውስጥ ተዛመተ። ዶርቃስ ከሞት ተነሳች!  በዚህ ተአምር ምክንያት ብዙ ሰዎች በጌታ አመኑ።

*የዶርቃስ ከሞት መነሳት ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 9፡ 36 – 43 ውስጥ ነው።*

Copyright picture courtesy of gospelservices.com

http://gardenofpraise.com